# የሰላም ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የሰላም ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

**ታህሳስ 2017 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

**ኢትዮጵያ**

# የሰላም ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች

ዶ/ር ሽኩር ሰይድ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

እጩ ዶ/ር አያና በየነ (ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ)

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

# ማውጫ


የሞጁሉ አጠቃላይ መግቢያ ........ 4
የሞጁሉ ዓላማ ........ 5
የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ ........ 5
የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5
የስልጠና ተተኳሪዎች ........ 6
የማስልጠኛ ግባዓቶች ........ 6
የማስልጠኛ ዘዴዎች ........ 6
ሞጁሉን ለማጠናቀቅ የሚወስደው ጊዜ ........ 7
ምእራፍ አንድ ........ 8
የሙስና ወንጀል ምንነት ........ 8

*1.2. መግቢያ ........ 8*

*1.3. የምእራፉ ዓላማ ........ 8*

*1.4. የተፈቀደው ሰዓት ........ 8*

*1.5. የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤ ........ 8*

*1.6. የሙስና ወንጀል ምንነት ........ 9*

*1.7. የሙስና ዓይነቶች ........ 10*

1.7.1. ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption) ........ 10
1.7.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption) ........ 11
1.7.3. ስርዓታዊ ሙስና (Systemic Capture) ........ 11
1.7.4. ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption) ........ 12

*1.8. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ........ 12*

1.8.1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት ........ 13
1.8.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት ........ 13
1.8.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም ........ 13
1.8.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር ........ 14
1.8.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ ........ 14
1.8.6. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ........ 15
1.8.7. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9) ........ 15
1.8.8. ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10) ........ 16
1.8.9. የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11) ........ 16
1.8.10. አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12) 16
1.8.11. የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13) 16
1.8.12. አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14) ........ 17
1.8.13. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15) ........ 17
1.8.14. በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16) ........ 18

1.8.15. በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17) ...... 18
1.8.16. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18) ...... 18
1.8.17. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19) ...... 19
1.8.18. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20) ...... 19
1.8.19. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21) ...... 19
1.8.20. የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22) ...... 20
1.8.21. መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23) ...... 20
1.8.22. መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24) 21
1.8.23. ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26) ...... 21
1.8.24. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25) ...... 21
1.8.25. ማቀባበል (አንቀፅ 27) ...... 21
1.8.26. በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28) ...... 22
1.8.27. በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29) ...... 22
1.8.28. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30) ...... 22
1.8.29. ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31) ...... 23
1.8.30. ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32) ...... 23
1.8.31. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33) ...... 23

*2.1. መግቢያ ...... 25*

*የተፈቀደው ሰዓት ...... 26*

*2.2. በሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ...... 26*

*2.3. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች ...... 28*

*2.4. በሰላም ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች ...... 30*

*2.5. የሙስና ስጋት ...... 33*

*2.6. የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና ...... 34*

2.6.1. ስልጣንን አላግባብ በመጠቀምና የሃብት ብዝበዛ ማካሄድ ...... 34
2.6.2. የሃብት ብዝበዛ ስጋት ተጋላጭነት ...... 34
2.6.3. የሀብት ቁጥጥር እና ክትትል አንጻር ...... 35
2.6.4. ከበጀት አያያዝ እና አጠቃቀም አንጻር ...... 35

*2.7. በሰላም ዘርፍ የሙስና መንስኤዎችና ጉዳቶች ...... 38*

*2.8. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ...... 41*

*2.9. በሰላም ሚኒስቴር የተስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ያስከተሉት ጉዳት ...... 42*

*2.10. በንብረት አስተዳደር ላይ የተስተዋለ ብልሹ አሰራርና ጉዳቶቹ ...... 46*

*2.11. ማጠቃለያ ...... 47*

*2.12. የማጠቃለያ ጥያቄዎች ...... 47*

**ምዕራፍ ሶስት** ........ 48
***የዘርፎች የሙስና መከላከያ*** ........ ***48***
**3.1. መግቢያ** ........ **48**
**3.2. ዓላማ** ........ **48**
**3.3. ስልጠናው የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ፤** ........ **49**
**3.4. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት** ........ **49**
**3.5. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን** ........ **49**
**4. የግል መገምገሚያ ቼክ ሊስት** ........ 55
**ማጣቀሻ** ........ 60

## የሞጁሉ አጠቃላይ መግቢያ

ይህ ሞጁል ስዘጋጅ ስልጣኞች በፀረ-ሙስና እና ብልሹ አሰራር ዙሪያ በሚያደርጉት ውይይት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚታዩ የብልሹ አሰራሮችን፣ የሙስና አይነቶች እና ምንጮቻቸውን፣ የሙስና መገለጫዎችና የመከላከያ ስልቶቻቸውን እንድሁም ሙስና እና ብልሹ አሰራር በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሰላም ግምባታ እና ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ልያስከትሏቸው የሚችሉ ጉዳቶችን እንድቃኙ ታስቦ ነው።

በአለም ታሪክ ውስጥ ሙስና የመንግስት እና የአስተዳደር ሥርዓት ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ከሰው ልጆች ጋር የኖረ እና ረጅም ዕድሜ ያለው ድርጊት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወድህ ግን የሙስና ወንጀል ትልቅ የዓለም አቀፍ ችግር እና ለድህነት፣ ለደህንነት እጦት፣ ለኢ-ፍትሐዊነት እና ለግጭት ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ባለፉት አስርት ዓመታት ጉዳዩ የአገር መሪዎች፤ የዓለም አቀፍ የገንዘብና የፖሊሲ ተቋማት፣ ኮርፖሬሽኖች፣ አክቲቪስቶች እና የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ስቧል።

በዚህ ዘመን ያሉት ጥናቶችና ርፖርቶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮ ባሻገር የደህንነትና የፖለትካ እንድምታ እንዳለው ያሳያሉ። በዚህም ምክንያት የሀገራትን እድገት በመገታት ዜጎች ለእንግልትና ለሰላም እጦት በመዳረግ እንደሚሰደዱ ያመላክታሉ። በጥኖቶቹ መሰረተት በተለያዩ ደረጃ የምገኙ ሀገር አቀፍ እና አለማቀፍ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሙስና ተጋላጭነታቸው እየጨመረ ይገኛል። ይሄም የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት አካታች፤ አሳታፉና ብቃት ያላቸውን ተቋማት እንዳይገነቡ በማድረግ ዘረፈ ብዙ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል (World Bank, 2014; transparency international, 2022)።

ሙስና በማህበረሰቡ የሰላምና የፍትህ እኩል ተጠቃሚነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ሙስና የሰላምና ደህንነት ስጋት ምክንያት ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ ሰላምና ደህንነት ከሌለ ዘላቂ ልማትን ማምጣት አይቻልም። ሙስና ማህበራዊ ቅሬታዎችን ያባብሳል፣ የመንግስትን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ ይከታል፣ የተረጋጋ እና ሰላማዊ የሆነ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር በማድረግ ሀገርን ስጋት ላይ ሊጥል ይችላል።

የሰላም ዘርፍ በውስጡ የሰላም ሚኒስቴር እና የብሄራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን ተቋማት የያያዘ ሲሆን ሁለቱ ተቋማት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተቋቋሙ ሲሆን ተቋማቱ በህግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር፣ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የሠላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና የንቅናቄ ስልቶችን በመንደፍ ስራ የመስራትና በፌዴራልና በክልሎች መካካል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሰረተ የመልካም ግንኙነት ማዕከል እንዲኖር እንዲያግዝ የተደራጀ ዘርፍ ሲሆን ይህን እውን እንዲሆን የህዝብ ሰላም መጠበቁን ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግስታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል። በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል ሠላም እንዲሁም የመተባበር ባህል እንዲዳብር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን ቀይሶ ይተገብራል፤ ከባህልና ከሀይማኖት ተቋማት ጋር በቅርበት በመስራት ሠላምን የማስፈን ስራ ይሰራል፤ ለሰላም መከበር ከተለያዩ ሀይማኖቶችና ዕምነቶች ተከታዮች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል።

## የሞጁሉ ዓላማ

የሞጁሉ ዓላማ በሁለት ዋና ዋና ቦታዎች የተከለ ሲሆን  እነሱም የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ እና ዝርዝር ዓላማዎች ናቸው።

## የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

- የዚህ ሞጁል ዋና ዓላማ ሰልጣኞች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በመረዳት እንድታገሉ አቅማቸውን መገምባት ነው።

## የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህንን ሞጁል ሰልጥኖ ከጨረሱ በኋል ሰልጣኞች፤

- አጠቃላይ የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፣
- በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣
- በሰላም ዘርፍ የሚስተዋሉ የተለያዩ የሙስና ውንጀሎችና መገለጫዎቻቸውን ይገልጻሉ፣

- በሰላም ዘርፍ የምስተዋሉ የሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ይታገላሉ፣
- በዘርፋቸው ለሚያጋጥሙ የምስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮች የመቆጣጠሪ እና የመከላከያ ስልቶን ይቀይሳሉ ወይም ይነድፋሉ፣
- በዘርፋቸው የሚስተዋሉ የሙስና ወንጀሎች እና ብልሹ አሰራሮችን ይገመግማሉ።

## የስልጠና ተተኳሪዎች

- የዚህ ስልጠና ተተኳሪዎች በሰላም ዘርፍ በሚገኙ ሁለት ተቋማት ማለትም በሰላም ሚኒስቴር እና የብሔራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን ውስጥ የሚያገለግሉ ሰራተኞ እና አመራሮች ናቸው።

## የማሰልጠኛ ግባዓቶች

ስልጠናዉን በአግባቡ ለማስኬድ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንደከተለው የቀረቡ ሲሆኑ እንዚህም፣

- የተመቻቸ የስልጠና አዳራሽ
- LCD ፕሮጀክተር
- ላፕቶፕ ኮምፒዩተር
- ፍሊፕ ቻርት
- ማርከር እና
- እስተሽኔሪ ማቴሪያሎች ናቸው።

## የማሰልጠኛ ዘዴዎች

በስልጠና ወቅት የሚከተሉ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ።

- የማነቃቅያ ጥያቄዎች (Brainstorming)
- አጭር ገለጻ
- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ዉይይት
- ጥያቄ እና መልስ

- በግል ጥያቄዎችን መስራት

## ሞጁሉን ለማጠናቀቅ የሚወስደው ጊዜ

- ይህንን ሞጁል ለማጠናቀቅ የሚወስደው ጊዜ 3 ቀናት ወይም 24 የሥራ ሰዓታት ነው፡፡

# ምእራፍ አንድ

# የሙስና ወንጀል ምንነት

## 1.2. መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው። ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል። በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው።

## 1.3. የምእራፉ ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

## 1.4. የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 8፤00 ሰዓት

## 1.5. የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።

## 1.6. የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው። ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመሰጠት አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል።

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር።

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ “... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች

ይጨምራል…" በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችሰ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.7. የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption) ፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፈላል፡፡

### 1.7.1. ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣

የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

### 1.7.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሸሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 “ከባድ የሙስና ወንጀል” ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

### 1.7.3. ስርዓታዊ ሙስና (Systemic Capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡

ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.7.4. ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption) ፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

## 1.8. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡ የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፧

### 1.8.1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### 1.8.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

### 1.8.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው። እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው። ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ

የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.8.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

"የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.8.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሸጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኑን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

### 1.8.6. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.8.7. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

- ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤
- የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤
- በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም
- ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.8. ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.9. የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.10. አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ ወይም አጣሪ፣ ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.11. የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.12. አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል።

### 1.8.13. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም ፦

የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.8.14. በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም

በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.15. በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦

ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.16. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ

ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉሳላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.17. *ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት* (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.8.18. *ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ* (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.19. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤

ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.20. የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.21. መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.22. መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.23. ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.8.24. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.25. ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.8.26. በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.8.27. በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል።

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል።

### 1.8.28. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

### 1.8.29. ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

### 1.8.30. ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ።

### 1.8.31. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## በሰላም ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት መንስኤዎች እና ጉዳቶቹ

### 2.1. መግቢያ

ከዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከያ ስልቶች አንዱ የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መለየትና መተንተን አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ተቋማት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጉም፣ በየጊዘው ደንብና መመሪያ የሚያሻሽሉ ቢሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንጻር ግን እምብዛም ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የሰላም ሚኒስቴር እና ሌሎች በዘርፉ ማለትም በሰላም ዘርፍ፣ የሚሰሩ ተቋማት ከዚህ የተለዩ አይደሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሰላም ሚኒስቴር እና ሌሎች በዘርፉ የሚሰሩ ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ጉዳዮችን መለየት አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማትን ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት እርምጃ መውሰድ ስለሚገባ ከወዲሁ በመለየት ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ወስኝ ከፊተኛ ሚና አለዉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሰላም ዘርፍ ያለው የሙስና መንስኤዎችና ዋና ዋና ጉዳቶቹ ተዳሰዋል፡፡ የሙስና መንስኤዎችና ጉዳቶቹ በሰባት ዋና ዋና የተጋላጭነት ስጋቶች ክፍሎች ለመዳሰስ የተሞከረ ሲሆን እያንዳንዳቸውን በደንብ ሊያብራሩ ይችላሉ የተባሉ አስረጅ ናሙናዎች ታክለውበታል፡፡ የሙስና ወንጀል በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና አከባቢያዊ ሕይወታችን ላይ የሚያስከትለው ስጋትና ጉዳት እጅግ ሰፊ ነው፡፡ ከኢኮኖሚ አንጻር ሲገመገም አጠቃላይ የአንድን ሀገር እድገት ወደኋላ የሚያስቀር ሲሆን ከማህበራዊ ሕይወት አኳያ ደግሞ የሕግ ግድፈትን በማስከተል የዜጎችን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት ነው፡፡ ከፖለቲካ ሕይወት አንጻር ስንመለከት ደግሞ የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነትን የሚጎዳ አካሄድ እና በአንድ ሀገር ውስጥ የሕግ የበላይነትን በመጣስ ሀገርና ህዝብን ለውስብስብ አደጋ የሚያጋልጥ አሰራር ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሰላም ዘርፍ ላይ ጎልተው የሚታዩ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች እና ጉዳቶቹ ትንተና ቅርበት ካላቸው አለማቀፋዊ እና ሀገራዊ ተዛማጅ ጽሁፎች ጋር ተዳሶ ቀርቧል፡፡

### የተፈቀደው ሰዓት

- ይህንን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተሰጠው ጊዜ 12፡00 ሰዓት ነው፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄ

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባጠገባቹህ ካለው ሰው ጋራ በመነጋገር መልስ ስጡበት፡፡

- በምትሰሩበት መ/ቤት ምን ያህል የሙስና ስጋት ተጋላጭነት አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?
- በመንግስት አሰራር ላይ ሙስና ምን ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከታላል ብላቹ ታስባላችሁ?
- የአንድን ሀገር እድገት እንድሁም ሰላምና መረጋጋትን ከማቀጨጭ አንጻር ሙስና ሊያስከትለው የሚችለው ጉዳት ካገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር አብራሩ፡፡

## 2.2. በሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ሥርዓታዊ ሙስና ከአመጽ እና ከግጭት በሚወጡ አገሮች ውስጥ ሥር የሰደደ ችግር ነው (Cheng & Zaum, 2013; Lindberg & Orjuela, 2014)፡፡ ሙስና ከግጭት በኋላ ካለው የሰላም ጥረት ጋር ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ግንኙነት አለው (ግሎባል የሰላም መረጃ ጠቋሚ፣ 2015)፣ ሙስና የኃሳ ግጭት ስጋትን ይጨምራል (Neudorfer & Theuerkauf, 2014)፡፡ በአጠቃላይ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ልማት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል (ኤዲት፣ 2003)፡፡ የብዙዎቹ የድህረ-ግጭት ሀገራት ደካማ ተቋማትን በመፍጠር የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለግል ጥቅም ለማዋል ለሚፈቅዱ ተግባራት ለሙስና ተስማሚ የሙስና መፈጠሪያ ስፍራዎች ናቸው (ስቬንሰን፣ 2005)፡፡

ሙስና፣ የፍትህ እጦት እና የተለያዩ ግጭቶችን በመፍጠር ወጣቶችን ወደ ህገወጥ ቡድኖች እንዲቀላቀሉ እድል ፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ ወጣቶች በሶማሊያ አልሸባብን፣ በአፍጋኒስታን ታሊባንን እቅፍ ውስጥ እንዲገቡ የሚገፋፉ ምክንያቶች እንደነበሩ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ሀገራቱ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ከሆነ ሙስና ጋር ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ በ2015 ሶማሊያ እና አፍጋኒስታን ከሰሜን ኮሪያ በመቀጠል የመጨረሻዎቹን ደረጃ ይዘዋል (Belloni, 2014)፡፡ ሙስና በሰላም ግንባታ ላይ ለመስራት የሚደረጉ ሙከራዎችን አቅም ያዳክማል (GIZ, 2020)፡፡ በሀገራት የሙስና

መስፋፋት ምክንያት ሙስናን የመከላከል፣ የመመርመር እና የወንጀል ተጠያቂነት ቀጥተኛ ተልእኮ የተሰጣቸው ተቋማት ውጤታማ ባለመሆናቸው ነው። ይህ ደግሞ የፀረ-ሙስና ተቋማቱ ሕገ መንግሥታዊ ከለላ እና ተቋማዊ ነፃነት ስለሌላቸው ነው። ሙስና ከብሔር ፖለቲካ ጋር ተያይዞ ለሰላም ትልቅ ስጋት ነው፣ ለሀገሪቱም ህልውና ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ አለው (ዘመላክ፣ 2017)።

ሙስና ግጭትንና አለመረጋጋትን ሊፈጥርና ሊያባብስ ይችላል። ሙስና የመንግስትን ውሳኔን በማዛባት የህዝብ አገልግሎቶችን የሚያበላሽ በመሆኑ ሙስና ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ቅሬታዎችን በተለይም የእኩልነት እና የፍትህ እጦት ስሜትን ሊያባብስ ይችላል። ለአብነት ያህል፣ በአረብ ጸደይ አመጽ፣ ሙስና ሰፊ ቅሬታዎችን የፈጠረ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፣ ይህም በተለያዩ መንግስታት ላይ ህዝባዊ ንቅናቄን አመቻችቷል (ቺብዋና፣ 2008)። ሙስና የመንግስትን አገልግሎት ከሚያቀርቡ ተቋማት ወደ ግል ጥቅም መጠቀሚያ የሚውል ተቋም ሊፈጥር ይችላል (አሚናል, 2006)። በሞሮኮ ውስጥ በሙስና ላይ የተደረገ ጥልቅ ጥናት እንዳመለከተው ሙስና የአገሪቱን ኢኮኖሚዊ፣ ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ብቃቷን አዳክሟል (ክሊትጋርድ, 1988)። በዚሁ መሰረት በጋና የተደረገ ሌላ ጥናት እንዳመላከተው ሙስና የጎሳ ግጭቶችን ያጠናክራል፣ የክልል እና የፌደራል ተቋማትን ግንኙነት በማበላሸት የመልካም አስተዳደር ችግር እንደፈጠረ አረጋግጧል።

በአለም ላይ ሙስናን በመዋጋት ከፍተኛ ውጤት ያመጡ እና ለሌሎች ሀገራት አርአያ መሆን የቻሉ ሀገሮች መካከል፦ የሲንጋፖር ፀረ ሙስና ተቋም በ1952 የሙስና ተግባራት ምርመራ ቢሮ (CPIB) ሲሆን በፀረ ሙስና ትግሉ ውስጥ የተገኘው ስኬት በዋናነት በሶስት ምክንያቶች እንደነበር ይገለጻል እነርሱም፦ ከመንግስት ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎት፣ በቂ የህግ ማዕቀፍ እና የተግባር ነፃነት (ኳህ፣ 2001) ናቸው። የሆንግ ኮንግ ፀረ-ሙስና ተቋም በ1974 የተመሰረተ ሲሆን ጥንታዊ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በጣም ስኬታማ ተቋም ነው። ገለልተኛው የሙስና ኮሚሽን (ICAC) በርካታ የቅጣት ውሳኔዎችን ያስገኙ የምርመራ ሪከርድ ገንብቷል (ሄይልብሩን፣ 2004)። በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የቅርብ ጊዜ የሙስና ግንዛቤ ኢንዴክስ መሰረት፣ ሆንግ ኮንግ በሙስና አነስተኛ ከሚባሉ የአለም ሀገራት ተርታ ትገኛለች። የሆንግ ኮንግ (ICAC) በግዛቱ እስካሁን የተንሰራፋውን ሙስና ለመግታት በተመሳሳዩ ምክንያቶች የተነሳ ውጤታማ ነበር (ማሪያ፣ 2002)። ከሆንግ ኮንግ እና ሲንጋፖር ቀጥሎ ኢንዶኔዢያ በፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎች ውስጥ የስኬት ታሪክ ሆኖ ተጠቅሷል። በ2002 የተቋቋመው የኢንዶኔዥያ የሙስና ማጥፋት

ኮሚሽን (KPK) በሙስና የተዘፈቁ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ 100% የሚጠጋ የቅጣት መጠን ላይ በመድረሱ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቷል (Transparency International, 2013)።

በ1990ዎቹ አጋማሽ የተቋቋመው የላትቪያ የሙስና መከላከል እና መዋጋት ቢሮ (KNAB) አሁን እንደ አውሮፓ በጣም ቀልጣፋ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተደርጎ ይቆጠራል። በከፍተኛ የፖለቲካ መሪዎች መካከል ያለውን ሙስና ለመመርመር ባሳየው ቁርጠኝነት ከፍተኛ አድናቆት ተችሮታል። ወደ አፍሪካ ስንመጣ የቦትስዋና የፀረ-ሙስና ተግባራት ታሪክ በጣም የሚያስመሰግን ነው። ሀገሪቱ ሙስና እና ሌሎች ተያያዥ ወንጀሎችን ለመከላከል በ1994 ዓ.ም የሙስና እና ኢኮኖሚክስ ወንጀሎች ዳይሬክቶሬትን መስርታለች። ቦትስዋና አሁን ከሰሃራ በስተደቡብ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ትንሿ ሙሰኛ ሀገር ሆናለች (Mail & Guardian Africa, 2014። ምንም እንኳን በኢንዶኔዢያ፣ በላትቪያ እና በቦትስዋና የፀረ-ሙስና ተቋማት የራሳቸው ልዩ ገፅታዎች ሊኖራቸው ቢችልም ለስኬታማነት ያበቃቸው እንደ ሆንግ ኮንግ እና የሲንጋፖር ፀረ ሙስና አካላት በጋራ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠራቸው ነው።

## 2.3. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች

ለአለም ሰላም አለመረጋጋት በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከነዚህም መካከል፦ (ሀ) የስራ አጥ ቁጥር መጨመር፣ (ለ) የህዝብ ፍላጎቶች አለመሟላት፣ (ሐ) የፖለቲካ መብቶች መከልከል፣ (መ) አግላይ በሆነ መንገድ ሀብትን ወደ ሌላ ቦታ የሚቀይሩ የታጠቁ ቡድኖች ወደ መንግሥት እንዲገቡ ወይም ሀብታቸውን እንዲያሳድጉ መፍቀድ ነው።

አብዛኞቹ ሙስና የተስፋፋባቸው አገሮች ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል ሙስናን የመመርመር ነፃነት ማጣት፣ ህብረተሰቡ ለሙስና ግድየለሽነት፣ በህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ውስጥ የተንሰራፋ ሙስና፣ ሙያዊ ብቃት እና ቁርጠኝነት ማነስ እና ሙስናን በመዋጋት ስትራቴጂካዊ አጋርነት አለመኖሩ ይገኙበታል (UNOCD, 2004)። የተለያዩ የማህበረሰብ ውይይቶችን ከፀረ ሙስና ጋር በማጣመር ግልፅነትና ተጠያቂነት ላይ በማተኮር ሰላምን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ሊደግፍ ይችላል። በማህበረሰቦች እና በተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት እንደገና በመመሥረት፣ በቡድኖች መካከል መተማመንን ለመገንባት፣ ግጭቶችን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት፣ በተቋማት ላይ እምነትን ለማደስ እና ማህበራዊ ተጠያቂነትን የማጎልበት አቅም አላቸው። የተሳለጠ ውይይት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ችግር ለመፍታት እና ከአስተዳደር መርሃ

ግብሮች ጋር በማጣመር ለዜጎች ጥያቄዎች እና ተጠያቂነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ፍላጎት ምለሽ ሊሰጥ ይችላል (ሆፐ-ኒሻንካ 2021b)።

የፀረ-ሙስና ተቋማት ውጤታማነት መስፈርቶች መካከል ተቋማዊ ነፃነት አንዱ ሲሆን በቂ ሀብቶች፣ ሁሉን አቀፍ ትእዛዝ፣ ግልጽነት፣ በቂ የምርመራ ሃይሎች እና ትብብርን ያጠቃልላል፡ ፡ ሙስናን መዋጋት ያለብን ዘርፈ ብዙ በሆነ ስልት ነው ምክንያቱም ተፈጥሮው፣ መጠኑ እና ቅርፁ ከቦታ ቦታ ስለሚለያይ ይህንን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች ስለሚለያዩ ነው (ሺመልስ፣ 2005)። በአለም ላይ ሁሉንም አገሮች የሚያስማማ አንድም ሞዴል ወይም አሠራር የለም (UNCAC፣ 2003)። ስለዚህ ሙስናን የመቆጣጠር ስትራቴጂ የችግሩን ስፋት፣ መንስኤዎቹንና ሙስና ሊፈጠር የሚችልባቸውን አካባቢዎች በግልፅ በመረዳት መጀመር አለበት (ሽመልስ፣ 2005)።

ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ስልቶችን ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት የፀረ- ሙስና ትግሉን የሚያደናቅፉ ዋና ዋና ችግሮች ወይም እንቅፋቶች መለየት አለባቸው (Wing-chi, 2014)። እነዚህን ችግሮች ለይተው ካወቁ በኋላ፣ አጠቃላይ የፀረ-ሙስና ስትራቴጂክ ዕቅዱን አውጥተው ወደ ትግበራ መተርጎም አለባቸው። ለዚህ ዓላማ እንደ ዊንግ-ቺ (2014) ያሉ ምሁራን፣ አንድሪው (2013)፣ ICAC (2009) እና እንደ ቶኒ ክዎክ ማን-ዋይ የቀድሞ የICAC ምክትል ኮሚሽነር ያሉ ባለሙያዎች የተለያዩ ሀገራት የሆንግ ኮንግ ሞዴል ICACን ስልቶችን እንዲከተሉ ይመክራሉ።

በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ የፖለቲካ ስርዓት መንግስታዊ በሆነ ኢኮኖሚ መያዝ፣ ለግል ጥቅም የሚያገለግል የፖለቲካ አመራር መኖር፣ አቅጣጫ የለሽ እና ውጤታማ ያልሆነ የመንግስት መዋቅር፣ ደካማ እና ለአደጋ የተጋለጡ ብሄራዊ የአስተዳደር ተቋማት፣ እንደ ፓርላማዎች፣ የፍትህ አካላት እና የሙስና ተቆጣጣሪ ተቋማት በኢትዮጵያ ለሙስና መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል (ከበደ፣ 2013)። በዚህ ጥናት መሰረት ተግዳሮት ናቸው ተብለው ከተገለጹት ችግሮች መካከል፦ የነጻነት እጦት፣ የሰራተኞች ውስንነቶች፣ የህዝብ አሉታዊ አመለካከት፣ ደካማ የህግ ማዕቀፎች እና የዳኝነት ሂደቶች ዘገምተኛ መሆን፣ በቂ የገንዘብ፣ የሰው እና የቴክኒክ ሃብት፣ የግልጽነት ጉድለት፣ ሰፊና ግልጽ የሆነ ስልጣን አለመኖር፣ በቂ የምርመራ ስልጣን እና ትብብር ማነስ፣ በቂ ያልሆነ ቅስቀሳ እና የዜጎች ተሳትፎ ማነስ፣ ለሙስና በቂ የሆነ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት ናቸው።

### 2.4. በሰላም ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች

የፌ/ሥ/ጸ/ሙ/ኮሚሺን በ2015 ዓ.ም. በሰላም ዘርፍ ሥር የሚገኙ ተቋማት ማለተም የሰላም ሚኒስቴር እና የብሔራዊ ተሀድሶ ኮሚሺን የሙስና ስጋት ተጋላጭነትን በዘላቂነት ለመፍታት በዘርፉ ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማቱ የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት በ10 ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል።

#### 2.4.1. የተቋም አደረጃጀት

ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በዘርፉ ካሉ ተቋማት የሰላም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስፈጻሚ ክፍል በማቋቋም 75% የሰው ኃይል ያሟላ መሆኑ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል ለባለሙያዎቹ በቂ ቢሮ እና ምቹ የሥራ ቦታ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደተፈጠረላቸው ጥናቱ ግልጽ አድርጓል። ከበጀት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ግን ክፍሉ ራሱን የቻለ የተመደበለት በጀት የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል። ነገር ግን ከሌሎች ክፍሎች ጋር በጋራ በመሆን እንደሚጠቀም በጥናቱ ተገልጿል።

በተቋሙ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ በማደራጀት ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል አጋዥ አጋዥ የስራ ክፍሎችን በማደራጀት እየሰራ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

የሰላም ሚኒስቴር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሲኪሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ምስጥራዊነቱን የጠበቀ አሰራር የዘረጋ እና ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት አግባብ የፈጠረ ቢሆንም የሕግ ክፍል በሚዘጋጁ ውሎች ላይ ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት እንደሚሰጥ አግባብ ወይም አከሄድ አለመኖሩ እንደ ክፍታት ተገልጿል።

ከተቋማዊ አደረጃጀት አኳያ የዘርፉ አዲስ ተቋማት የስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ ፈጥኖ ያለመግባት፣ ተቋማት የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሉ ራሱን የቻለ የተመደበለት በጀት አለመኖሩ እና በበቂ የስው ሃይል ባለመሟላቱ ስራውን በውክልና እንዲሰራ መደረጉ፣ ዘርፉ ለስነምግባር ግንባታ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ተግባር ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ እንዲሁም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሃብት ወይም ንብረት እንዲመዘበር፣ እንዲወሰድ፣ ወይም እንዲጠፋ ሊያደርግ ይችላል።

### 2.4.2. ተጠያቂነት

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው። ከዚህ አኳያ በወቅቱ በተደረገ ጥናት ተጠያቂነትን በተመለከተ የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል።

- ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር ጥናት ከማካሄድ አንፃር በሠላም ሚኒስቴር የአሰራር ስርአት ጥናት ያካሄደ እና ጥናቱን ተመርኩዞ የማሻሻልና የማረም ስራም የተከናወኑን ቢሆንም የደንበኞች እርካታን በተመለከተ በገለልተኛ አካል አለመጠናቱ እና የሥነምግባር መመሪያ (Code of conduct) አለማዘጋጀታቸው እንደ ክፍተት ተገልጿል።
- በተጨማሪም በዘርፉ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት በሚደርሱ ጥቆማዎች መሰረት ቅድመ-መከላከል ስራ አለመኖሩ እንደ ክፍተት ተገልፃዋል።
- የተቋማትን ተጠያቂነት ከማረጋገጥ አንፃር የስነ ምግባር መከታተያ ክፍል ለብቻው ትኩረት ተሰጥቶ አለመገምገሙ ክፍሉ ያሉበትን የአሰራር ክፍተቶች ለይቶ እንዲያውቅ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል አቅም እንዳይኖረው የሚያደርግ መሆኑ እንደ ሌላ ክፍተት ተጠቅሷል።
- በተጨማሪ የደንበኞችን እርካታ በገለልተኛ አካል አስደገፎ ያለማስጠናቱ በተቋሙ ያለውን የደንበኞች አገልግሎት ሁኔታ፣ የአሰራር ክፍተቶችን እና ተቋሙ በደንበኞች አገልግሎት ዙሪያ የማሻሻያ ስራ እንዳይሰራ የሚያደርግ መሆኑን ተገልጿል።

### 2.4.3. የንብረት አስተዳደር

ይህንን በተመለከተ በዘርፉ ካሉት ተቋማት የሰላም ሚኒስቴር የተለያዩ የንብረት አስተዳደር እና መቆጣጠር ስርዓትን የሚኪተል ብሆንም የካይዘን ስርአት አለመተግበሩን በጥናቱ እንደ ክፍተት ተገልጿል።

### 2.4.4. የግዥ አስተዳደር

የግዥ አስተዳደርን በተመለከተ አሁንም በዘርፉ ካሉት ተቋማት የሰላም ሚኒስቴር የግዥ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ካሉት የሥራ ክፍሎች ጋር

ምክክርና ርፖርት የሚያካሄድ ቢሆንም አልፎ አልፎ በዕቅድ የማይገዙ መኖራቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም እንደ አንድ የአሰራር ክፍተት በጥናቱ ተሰተውሏል። እንድሁም በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ የሚገዛበት አካሄዶችም እንደነበሩ ጥናቱ ይጠቅሳል። በሌላ በኩል ከገዥ አሰተዳደር አኳያ በዘርፉ ብዙ ቁጥር የሚይዘው ግዥ የሚፈጸመው በፕሮፎርማ መሆኑ ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭነት ያለው እድል ሰፊ መሆኑን ጠቅሶ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ሊቀንሱ የሚችሉ የግዥ ዘዴዎችን መጠቀም መጠቀም እንደሚገባቸው በጥናቱ አቅጣጫ ተቀምጧል።

### 2.4.5. የሰው ሀብት አስተዳደር

ለአንድ ተቋም የስራ ውጤታማነት የሰው ሀብት አስተዳደር ቁልፍ የስራ ክፍል መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር በዘርፉ ካሉት ተቋማት የሰላም ሚኒስቴር የአስተዳደር ኮሚቴዎች ማለትም የቅጥር፣ የዲሲፕልንና የዝውውር ኮሚቴዎች የተደራጁ መሆኑን በጥናቱ ቢረጋገጥም ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችንና የሥራ ልምዶችን ከማጣራት እና የሥራ አመራር ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ እንዲሁም የሙያ ብቃት ማጎልበቻና የሥነ ምግባር ማሻሻያ ስልጠናዎች ለአመራሮችና ሰራተኞች መሰጠቱን የሚገልፅ መረጃ አለመኖሩ እንደ ስጋት ተጠቅሷል።

በተጨማሪም የሰው ሀብት መረጃቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለማደራጀታቸው በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። ከሰው ሀብት አስተዳደር አኳያ የተለዩ ክፍተቶች፡ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችንና የሥራ ልምዶችን ከማጣራት እና የሥራ አመራር ምደባ በውድድር ከማድረግ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶት የማይሰራ መሆኑ እና የሰው ሀብት መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደራጀ መሆኑ በዘርፉ እንደስጋት ተወስዷል።

### 2.4.6. የሀብት ምዝገባ

የሀብት ምዝገባ መረጃን በተመለከተ በዘርፉ ከአምስት አመራሮች አራቱ፣ ከሁለት መቶ ስልሳ አራት ሰራተኞት ሁለቱ በድጅታል የሀብት ምዝገባ ስርአት ሀብታቸውን ያስመዘገቡ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ከሀብት ምዝገባ ስርዓት ጋር በተያያዘ የታዩ ክፍተቶች፡ በዘርፉ ያሉ የተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሁሉም እንድያስመዘግቡ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ እንደስጋት ተወስዷል።

### 2.4.7. የኦዲት ቁጥጥር

በዘርፉ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በየሩብ አመቱ እየተዘጋጀ የሚቀርብ እና በኦዲት ግኝቶች ላይ የተቋሙ ማኔጅመንት ውይይት በማድረግ ተግባራዊነታቸው ላይ ክትትል እና ድጋፍ የሚያደርጉ እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቶች ለሁሉም የሥራ ክፍሎች ተደራሽ የሚደረጉ ቢሆንም የቀረበው የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እንደሚያሳየው ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 60,982,374.25 መሆኑን መረጃዎች ሲያሳዩ የተቋሙን የውጭ ኦዲት ሪፖርት ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በኦዲት ቁጥጥር አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች፡ የኦዲት ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊነት ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ለሙስናና ብልሹ አሰራር መንገዶችን የሚከፍቱ መሆናቸው አያሻማም፡፡

## 2.5. የሙስና ስጋት

የፌ/ሥ/ጸ/ሙ/ኮሚሽን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያከሄደውን የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መንሴ በማድረግ በዚህ ክፍል ውስጥ የሰላም ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ ክፍሎችና ሂደቶች መደበኛ ስራቸውን ሲያከናውኑ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን የመለየት፣ የመከሰት ዕድሎቻቸውን እና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽዕኖ በደረጃ (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ) በማለት በማስቀመጥ በመጨረሻም የሙስና ስጋት ትንተና ተካሄዷል፡፡

የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መካከለኛና ከባድ በመባል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው ሙስና በስራ ክፍሎች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የግዢ እና ፋይናንስ፣ መሰረታዊ አገልግሎት እና የሀይማኖት ምዝገባ የስራ ክፍሎች ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው ክፍሎች መሆኑን በጥናቱ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የሰው ሃብት ስራ ክፍል አነስተኛ የሆነ ሙስና ስጋት እንዳለበት ከጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 2.6. የሰላም ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች | የመከሰት እድል | ቢከሰት የሚያመጣው ተፅኖ | የሙስና ስጋት | የስጋት መንስኤዎች | የመፍትሄ ሃሳቦች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ግዢ እና ፋይናንስ | ከፍተኛ | ከፍተኛ | ከባድ | የግዢ አዋጁ | በቴክኖሎጂ የታገዘና ግልጽ |
| 2. | መሰረታዊ አገልግሎት | መካከለኛ | ከፍተኛ | ከባድ | ንብረት | |
| 3. | ሰው ሀብት | ዝቅተኛ | መካከለኛ | አነስተኛ | አስተዳደር ምደባ እና | |
| 4. | የሀይማኖት ምዝገባ | መካከለኛ | ከፍተኛ | ከባድ | አመዘጋገብ | |

### 2.6.1. ስልጣንን አላግባብ በመጠቀምና የሃብት ብዝበዛ ማካሄድ

በየትኛውም የሚኒስቴር መ/ቤት ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በተለያዩ መንገድ ለሙስና በር ይከፍታል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት ኃሳቦች በሰላም ሚኒስቴር ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም እንዴት አድርጎ ሙስናን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የሚገልጹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ የመንግስት እና የሕዝብን ሃብትና ንብረት ያለአግባብ ሲመዘበሩ እና ሲበዘበዙ ይታያል፡፡ ከዚህ አንጻርም የሰላም ሚኒስቴር በተለያዩ የአሰራር ሥርዓት ውስጥ ችግሮች እንደሚያጋጥሙት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ሙስና ክፍል ያካሄደው የዳሰሳ ጥናት ያሳያል፡፡ ይህንን በተመለከተ ቀጥሎ ከቀረበው ሃሳብ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ምን ዓይነት የሙስና ወንጀል ተጋላጭነት ስጋት እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.6.2. የሃብት ብዝበዛ ስጋት ተጋላጭነት

በሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ የመንግስት እና የሕዝብን ሃብትና ንብረት ያለአግባብ ሲመዘበሩ እና ሲበዘበዙ ይታያል፡፡ ከዚህ አንጻርም የሰላም ሚኒስቴር በተለያዩ የአሰራር ሥርዓት

ውስጥ ችግሮች አጋጥሞት ታይቷል። ይህንን በተመለከተ ቀጥሎ ከቀረበው ሃሳብ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ምን ዓይነት የሙስና ወንጀል ተጋላጭነት ስጋት እንዳለ መረዳት ይቻላል።

### 2.6.3. የሀብት ቁጥጥር እና ክትትል አንጻር

የሰላም ሚኒስቴር የተለያዩ ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ የመንግስት ንብረቶችን እንደሚያስተዳድር በግልጽ የታወቀ ነው። ከዚህ አንጻር የተሽከርካሪዎችን ቁጥጥር፣ ክትትል እና ስምሪትን በተመለከተ ክፍተቶች እንዳሉና ለሙስና ስርዓት የተጋለጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያስረዳሉ።

### 2.6.4. ከበጀት አያያዝ እና አጠቃቀም አንጻር

ከፊተኛ የመንግስት አመራሮች ለሥራው ቅርበት ያላቸውን እና በቅጥታ ሥራው የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች ወይም ሰራተኞችን ወደ ጎን በመተው ለበዓል መዋያ እና ለተለያዩ ጉዳዮች አበል ለማግኘት ስባል ብቻቸውን በመስክ ሥራ ላይ ይሰማራሉ። ይህ ድርጊት የሀገርን ሀብት ከታሰበለት ዓላማ ወደ ሌላ በማዞር ተቋማዊ ብቃትንና ሞራልን ይጎዳል።

## አስረጅ ናሙና 1

በሰራተኛ መድረክ ላይ የተነሱ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ ክፍል በ2016 ዓ.ም. ባካሄደው የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት መሰረት በአንድ ወቅት በሰላም ሚኒስቴር ውስጥ በነበረ ሁኔታ በአገልግሎት ውስጥ ወሳኝ ስራዎችን ለሚሰሩ ባለሙያዎች የውጭ ሀገር የጉዞ እድሎች ይመጣሉ። የጉዞው ዋነኛ ዓላማ እነዚህ ባለሙያዎች ለሙያ እድገታቸውም ሆነ ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ አገልግሎት ሰፊ ዓላማ የሚጠቅሙ ልምድ እንዲቀስሙ እና ዕውቀት እንዲያገኙ ታስቦ ነበር። ይሁን እንጂ ስልጣናቸውን ተገን በማድረግ ኃላፊዎች የጉዞ እድሉን ከማሳወቅ ይልቅ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች በመደበቅ እና ከጉዞው ጥቅም ማግኘት የሚገባቸውን ሰዎች በማሳጣት እድሉን ለግል ፍላጎትና ጥቅም እንዳዋሉ የዳሰሳ ጥናቱ ይገልጻል። በተጨማሪም ኃላፊው ጉዳዩ የማይመለከተውን ሰው የጉዞው ተጠቃሚ በማድረግ ተሳታፊው ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ወይም ዶላር እንዲያገኙ እንዳደረጉም በጥናቱ ተገልጿል።

ይህ ጉዳይ በአገልግሎቱ ውስጥ ሥልጣንንና ሀብትን አላግባብ መጠቀሙን የሚያሳይ ሲሆን ይህም የሥነ ምግባር ብልሹነት፣ ተጠያቂነትን እንዲሁም በመ/ቤቱ ሰራተኞች ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ ስጋት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ድርጊቶች የመንግሥት ባለሥልጣናት ሥልጣናቸውን ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ሌሎችን በክንቱ የሚጠቅሙባቸውን የሙስና ጉዳዮች ይበልጥ መሰረታዊ በሆነ መንገድ እንደሚያነሳሱ ይጠቁማሉ፡፡

ይህንን እንደ መነሻ ሀሳብ በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያዩ!

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. **ስልጣንን አላግባብ ከመጠቀም አኳያ**

   - ኃላፊው እድሉን ከሚገባቸው ባለሙያዎች ለመከልከል መወሰኑ ስልጣንን አላግባብ ከመጠቀም አንጻር እንዴት ታዩታላቹ? እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በአንድ የሕዝብ ተቋም ውስጥ የሚያስከትለው ሥነ ምግባራዊና ሕጋዊ ተጽዕኖ ምንድን ነው ብላቹ ታስባላቹ?

2. **ድርጅታዊ ተዓማኒነት ላይ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ አንጻር**

   - ይህ ዓይነቱ ሙስና የሰላም ሚኒስቴር በሞራል፣ በመተማመንና በአጠቃላይ የአሰራር ሥርዓት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል? እንዲህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች ተአማኒነትንና የሕዝቡን አመኔታ ሊያዳክሙ የሚችሉት እንዴት ነው?

3. **አድሎ እና የግል ጥቅም ከማግኘት አንጻር**

   - ተሳታፊውን ወደ ጉዞው ማምጣታቸው በዚህ ሁኔታ ምን ዓይነት ምግባረ ብልሹነት ያሳያል? በውሳኔ ሂደት ረገድ አድልዎ ማድረግ፣ ተገቢ ባልሆነ መንገድ አጋጣሚዎችን ማግኘት የሚጨምረው እንዴት ነው?

4. **ሥነ ምግባራዊ ተጠያቂነት**

➢ በመንግስት ሚኒስቴሮች ውስጥ ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ ተጠያቂነትና ግልፅነት ለማረጋገጥ ምን ዓይነት አሰራሮች መካሄድ አለባቸው ብላቹ ታምናላቹ? የበላይ ተመልካች አካላት እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን እንዴት መፍታት ይኖርባቸዋል ብላቹ ታስባላቹ?

## 5. የስርዓተ-ምህዳር መፍትሄዎች

➢ በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶችን ለመቀነስ ምን ዓይነት ስርዓታዊ ተሃድሶ ወይም መከላከያ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል ብላቹ ታስባላቹ?

**ማስታወሻ**

በዚህ ድርጊት ውስጥ ከሚስተዋሉ የሙስና ወንጀሎች በዋናነት የሚጠቀሰው የመንግስት ወይም የሕዝብን ሀብት አላግባብ መበዝበዝ ስሆን በመስክ ሥራው ለሚሰማሩ አመራሮች ደግሞ ገንዘብን ያለአግባብ መውሰድን ያሳያል:: ለሕጋዊ ወጪዎች የሚመደበውን ገንዘብ በተሳሳተ መንገድ እየተዘዋወረ ለሌላ ዓላማ ይውላል::

በሌላ በኩል ስልጣንን አላግባብ የመጠቀም ብልሹ አሰራርንም በዚህ ውስጥ እናያለን:: ምክንያቱም ባለስጣናት ስልጣናቸውን አላግባብ በጠቅም የገንዘብ ተጠቃሚ ይሆናሉ:: እንድሁም የማጭበርበር ምግባረ ብልሹነት እና ሙስና በዚህ ውስጥ ይታያል:: ባለስልጣናቱ የሚፈልጉትን ገንዘብ ለማግኘት በተሳሳተ መንገድ አስተዋፅዖ እንደ ነበራቸው በማስመሰል እና ማስረጃ በማቅረብ ሁኔታውን ሊያበላሹ ይችላሉ::

ይህንን ድርጊት ሙስና ከሚያሰኟቸው ዋና ዋና ተግባራት ጥቅቶቹ አንደኛው የመንግስትን ሀብት ለግል ጥቅም ስባል መበዝበዝ ስሆን ለሥራው አስተዋፅዖ ያላቸውን ግለሰቦች ወጭ ለመሸፈን የሚወጣው በሌላ መንገድ አመራሮች የውሎ አበል ለማግኘት ስባል ብቻ በሥራው ጣልቃ ስገቡ የመንግስትን የውጭ ደረጃ ከመጠን በላይ ከፍ ያደርገዋል:: ሁለተኛው ኢፍትሃዊ የሆነ የኃብት ክፍፍል ስሆን የመስክ ስራን እና ተያያዥ የሆኑ የገንዘብ ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ እነዚህ እድሎች ብዙውን ጊዜ ውስን ከመሆናቸው የተነሳ ሰዎች እኩል ተጠቃሚ አይሆኑም:: ባለስልጣናት እነዚህን እድሎች ብቁ ከሆኑ እና ለሥራው በቀጥታ አስተዋፅዖ ከሚያደርጉት ባለሙያዎች ስነጥቁ የፍትሃዊንት እና የብቃት መርሆችን ይጥሳል::

ሌላኛው ተቋማዊ ዓላማዎችን የሚያበላሽ ስሆን እንደ ምርምር፣ ክትትል ወይም የፕሮግራም አፈጻጸም እና የመሳሰሉ የተወሰኑ ግቦችን ማሳካት አይቻልም። ምክንያቱም የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት ስባል ብቁ ያልሆኑ ባለስልጣናትን በማሳተፍ የተቋሙ አላማ ወደ ጎን በመተው አጠቃላይ አቅሙን እና ውጤታማነቱን ያዳክማል።

እንደነዚህ አይነት አሰራሮች የሥራ ውጤታማነትን ይቀንሳሉ፣ የፋይናንስ ክሳራን ያስከትላሉ፣ ብቃት ያላቸውን ሰራተኞች ተነሳሽነትን ያግዳሉ፣ ተቋማዊ አለመተማመንን ያስከትላሉ፣ ደካማ ተጠያቅነትና አስተዳደርን ያስከትላሉ፣ የሙስና ባህልን የሚያበረታቱ ስሆን ከሰፊው ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ አንጻር ደግሞ ስታዩ ደካማ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለዩነቶችን ማሰፋት እና የድርጅቱንና የተቋሙን ግቦችን ያዳክማል።

ባጠቃላይ ባለሥልጣናት በውሎ አበል አማካኝነት የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት ሲሉ ብቻ በመስክ ሥራ ሲካፈሉ ሥልጣንን እና ገንዘብን አላግባብ መጠቀምን በግልጽ ያሳያል። ይህ ዓይነቱ ሙስና የተቋሙን ገጽታ ያበላሻል፣ ውጤታማነቱን ይቀንሳል፣ ሰራተኞችን እና ሀብቱንም ያባክናል። ሁሉም በድርጅቱ ውስጥም ሆነ በሰፊው ህብረተሰብ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ።

## 2.7. በሰላም ዘርፍ የሙስና መንስኤዎችና ጉዳቶች

***የማነቃቂያ ጥያቄ***

ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሃሳብ ላይ ያላችሁን አስተያየት ግለፁ።

- *ሙስና በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ ግንኙነት እና በአገር ደህንነት ላይ የሚያስከትላውን ስጋትና ጉዳት ዘርዝሩ።*

*ሙስና በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ከባቢያዊ ሁኔታዎች የሚያደርሰው ጉዳት ዘርፈ ብዙ ነው።*

| የጉዳት ዓይነቶች | ዝርዝር ማሳያዎች/መገለጫዎች |
| --- | --- |

| | |
|---|---|
| **ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች** | ➢ የግብር አሰባሰብ ስርአትንና ደንብን በማዛባት ከገቢ ግብር እና ልዩ ልዩ ቀረጥ ገቢዎች ለመንግስት መግባት የሚገባውን በመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ የመንግስት አገሌግልቶች የተዳከመ እንዱሆን ያደርጋል፡፡<br>➢ በመንግስት ለኢኮኖሚ እዴገት የተነደፈ የሌማት ፕሮጀክቶች ለህብረተሰቡ የጎሊ ጥቅም በማይሰጡ ፕሮጀክቶች እንዲተኩ ያደርጋል፡፡<br>➢ ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስተሮችን (ባለሀብቶችን) የመንግስት አገልግሎቶችን ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ በማድረግ/በማስገደድ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ይገድባል፡፡<br>➢ ኢፍትሃዊ በሆነ አስተዳደር የሰራተኛውን እድገት፣ ቅጥርና ጥቅማ ጥቅም ችሎታን መሰረት ባደረገ መንገድ ባለማከናወንና የሰራተኛውን የስራ ፍላጎትና ሞራል እጅጉን እንዲጎዳና ምርታማነት እንድቀንስ ያደርጋል፡፡ |
| **ማህበራዊ ጉዳቶች** | ➢ አብዛኛውን ህዝብ ለድህነት ይዳረጋል፡፡ ሰርቼ የተሻለ ኑሮ እኖራለሁ ብሎ የሚመኘው ህዝብ ሰርቶ የመኖር ምኞቱን በማጨለም ከፍተኛ የሞራል ውድቀት እንዲደርስበት ያደርጋል፡፡ ለስራ አጥነት፣ ለጎዳና ተዳዳሪነት እና ለሴተኛ አዳሪነት ያጋልጣል፣ እጅግም ሲከፋም ለስደት ይዳርጋል፡፡<br>➢ በህግ ፊት በእኩልነት የመዳኘት መብትን በመጣስ ማህበረሰቡን ላልተረጋጋ ህይወት በመዳረግ፣ ዋልጌነት፣ ጥፋተኝነትና ስርአተ አልበኝነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በዚህም የህዝቡ ሰላማዊ ኑሮ አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡<br>➢ ለማህበራዊ አገልግሎት፣ ለትምህርትና ለመሰረተ ልማት ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ መዋል የሚገባው የመንግስት ሃብት ለጥቂቶች እንዲውል ያደርጋል፡፡ |

| | |
|---|---|
| **ፖለቲካዊ ጉዳቶች** | ➢ ዜጎች በሀገራቸው ሀብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ የተዛባ የሀብት ክፍፍል እንዲፈጠር፣ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው፣ በመንግስት ላይ የሚኖራቸው እምነት እንዲሸረሸርና፣ በመንግስትና በህዝብ ዘንድ ትልቅ ክፍተት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ በማበርከት የፖለቲካ አለመረጋጋት ያጋለጣል፡፡<br>➢ የህግ የበላይነትን በማደብዘዝ ስርአተ አልበኝነትንና የዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ህዝቡ የተረጋጋ ማህበራዊ ኑሮ እንዳይኖር ከማድረግ ባሻገር አንደ መንግስት በመንግስትነቱ እንዳይቀጥል ምክንያት ይሆናል፡፡<br>➢ በመንግስት ላይ የተለያዩ ተቃውሞዎች እንዲነሱ በማድረግ በከፋ መልኩ ለጎሳ፣ ለብሄሮችና ለሃይማኖት ግጭቶች በር ይከፍታል፡፡ |
| **አካባቢያዊ ጉዳቶች** | ➢ የተፈጥሮ ሀብቶች ሀላፊነት በጎደለው መንገድ በመመዝበር ለአካባቢ ብክለት መጋለጥ ይዳርጋል፡፡<br>➢ የደን ልማት ቦታዎች እንዲጨፈጨፉ፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ሀብቶች እንዲሰረቁ፣ ወደአገር ውስጥ እንዳይገቡና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ኬሚካልች ወደአገር ውስጥ እንዲገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በመፍቀድ የሀገር የተፈጥሮ ሀብት እንዲባክንና እንዲመረዝ ያደርጋል፡፡ |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው ዳኛው፣ አቃቤ ህጉ፣ ፖሊሱ፣ ታክስ ሰብሳቢው፣ ቀረጥ ሰብሳቢው፣ ደህንነቱ፣ መከላከያው፣ የጤና ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት ወዘተ በሙስና የተዘፈቁ ከሆነ በአገር ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ከሁሉም አይነት ወንጀሎች የከፋ እና አደጋውም ከፊተኛ የሆነ መሆኑን ነው፡፡

## 2.8. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

***ማነቃቂያ ጥያቄ***

ከጎናችሁ ካሉ ሰልጣኞች ጋር በመወያየት ቀጥሎ በቀረበው ላይ ሃሳብ ስጡ፡፡

- የሙስና ድርጊትን (ወንጀሌን) ከሌሎች ወንጀሎች ማለትም (ግድያ፣ ሌብነት፣ ዝርፊያ) የመሳሰሉት ወንጀሎች የሚለየው በምንድነው ብለው ይገምታሉ?

ሙስና እንድስፋፋ እንዲሁም የመከላከልና የመቆጣጠር ስራውን አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉት ለየት ያሉ ባህርያት አሉት፡፡

### 1. የሙስና ወንጀል አፈጻጸም ስልት

የሙስና ወንጀል እንደ ሌሎች ወንጀሎች (ለምሳሌ፦ የግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ የአስገድድ መድፈር፣ ወዘተ) በስሜታዊነት የሚፈጸም ሳይሆን የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም በመሆኑ በደንብ ታቅዶበት የሚሰራና ለምርመራ መነሻ የሚሆን ምልክት እንዲህ በቀላሉ እንዳይገኝበት ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡

### 2. በወንጀለ ተጎጂው የሚሆነው መጎዱቱን ለማወቅ የሚቸገርበት፣ በወንጀል ተሳታፉዎች ሁሉ ተጠቃሚዎች መሆናቸው

በሙስና ወንጀል እንደሌሎች ወንጀሎች (ግድያ፣ ሌብነት፣ ዝርፊያ ወዘተ) አንዱ አጥቂ አንዱ ተጠቂ አይደለም፡፡ "**ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል**" የሚለው አባባልም ይህንን የሚያስታውስ ነው፡፡ ወንጀሉ የሚፈጸመው እጠብቀዋለሁ ብሎ በአደራ በተቀበለው ሰው በመሆኑ (የወንጀል ተጠቂ ህዝቡ ምን እንደተሰራ ሊያውቅ የሚችልበት እድል አነስተኛ በመሆኑ)፣ በወንጀሉ ተሳታፊ የሆኑት ሁሉ ተጠቃሚዎች በመሆናቸው (ጉቦ ሰጪና ጉቦ ተቀባይ) ወንጀሉ ሳይታወቅና ሚስጥር ሆኖ የመዝለቁ ሁኔታ ከፊተኛ ነው፡፡ ወንጀሉን ሊያጋልጥ የሚነሳሳውም በራሱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሳይሆን ለህብረተሰቡ ካለው ተቆርቋሪነት ተነስቶ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡

### 3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣናት የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማግለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀል ተሳታፊ የሚሆኑት አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው። እነዚህ የመንግስት ባለስሌጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀል እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ በተቻለ አቅም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ የሚሰጣቸው ነው።

## 2.9. በሰላም ሚኒስቴር የተስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አስራሮች ያስከተሉት ጉዳት

በኢትዮጵያ በመንግስት አስተዳደር እና የሕዝብ አገልግሎት ዘርፍ ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን አንዳንድ ጥናቶች ያሳያሉ። መንግስትና ሕዝብን በታማኝነት እንድያገለግሉ በአደራ የተሰጣቸውን ኃላፊነት የመንግስት አካላት በሚገባ በተደራጀ መልኩ በሙስና ድርጊት የሚሳተፉ መሆናቸውን አግባብነት ባለው መልኩ እያገለገሉ አለመሆናቸውን ጥናቶቹ ያሳያሉ። የፀረ-ሙስና ሥርዓቱም እስካሁን ሙስናን በመቆጣጠር ረገድ ሕጎቹ እና ተቋማቱ ውጤታማ እንዳልነበሩ ይገልጻሉ። በመንግስት የተለያዩ ዘርፎች የሚደረገው ሙስና በማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ልማትና አስተዳደር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል (Degye, Arega, and Demirew, 2024)። በኢትዮጵያ የሙስና ወንጀል በተለያየ መልኩ የሚከሰት ሲሆን ለምሣሌ ያህል የሚጠቀሱት በዝምድና መስራት፣ ህዝብን መጠቅሚያ ማድረግ፣ ፖሊሲዎችን ማዛባት፣ በመንግሥት ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ የሚፈፅሙ የግል ጥቅሞች መሰረት ያደረጉ ወዘተ ናቸው። ምንም እንኳን የፀረ-ሙስና ህጎች በሀገሪቱ ውስጥ  በመርህ ደረጃ ጠንካራ ቢሆንም ግን በበቂ ሁኔታ አልተተገበሩም። በ2019 በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በተዘገበው የሙስና አስተሳሰብ ማውጫ መሠረት ኢትዮጵያ ከ180 አገሮች ውስጥ 96ኛ፣ በ2020 ደግሞ 94ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች (TI, 2019 & 2021)።

በሌላ በኩል እንደ Similarity Gain Integrity report ምንም እንኳ በተመሳሳይ ቀጠና ካሉት ሀገሮች ያነሰ ደረጃ ቢኖራትም ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ሙስና እንዳለ አመልክቷል (GAIN-Integrity, 2017)። የ2019 TRACE Bribery Risk Matrix አስተዋጽኦ ስለሚያደርጉ ነገሮች በንድፈ ሐሳብ መሰረት ኢትዮጵያን በከፍተኛ አደጋ ምድብ ውስጥ አስቀምጧታል። ጥናቱ ከተካሄደባቸው ከ200 ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ በ176ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በ2018

Transparency International ባስቀመጠው መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሙስና በከፊታኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ ተቋማት የኃይል ዘርፍ፣ ዳኝነት፣ ፖሊስ፣ የመሬት አስተዳደር፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች (ጤና እና ትምህርት) ናቸው። ከሕግ እና የተቋማት ማዕቀፍ አንጻር ኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል በ2003 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስምምነት የተፈራረመች ስሆን በ2007 ዓ.ም. ደግሞ አጽድቋለች። በተጨማሪም ሀገሪቱ አፍሪካ ሕብረት ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ኮንቬንሽን በ2004 ዓ.ም ፈርማ በ2007 ዓ.ም. አጽድቋለች። ሙስና የማህበራዊ ቅሬታዎችን በማባባስ የመንግስትን ስርዓት ያበላሻል፣ የተረጋጋ እና ሰላማዊ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር በማድረግ የህዝብ አገልግሎቶችን ሊያጓድል ይችላል። የጸረ-ሙስና አካሄዶች ሰፊ የሆነ የሲቪክ ማህበራት እና የዜጎች መብቶች ላይ ያነጣጠረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲሁም መረጃ የማግኘት መብት እና የመንግስት ግልጽ አቀራረቦችን ያካትታሉ (BMZ እና ሌሎች 2019)። ሙስና የህዝብ ቅሬታዎችን እና የፖለቲካ ለውጥ ጥያቄዎችን ይጨምራል (Mauro, 1995)።

የእንደዚህ አይነቱ የሙስና አሰራር በሰራተኞች፣ በተቋማት እና በሀገር ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ሲሆን እነዚህም፦

1. **ድርጅታዊ አመኔታ መሸርሸር፦** ሠራተኞች ወይም ሌሎች ባለድርሻ አካላት እድሎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ አለመሰራጨቱን ሲገነዘቡ በድርጅቱ አመራር ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል። ሠራተኞች የሚያደርጉት ጥረት ተቀባይነት ወይም መልካም ውጤት ላያስገኝላቸው ስለሚችሉ ተስፋ ሊቆርጡ፣ ግራ ሊጋቡና ጥሩ ውጤት ሊያገኙ እንደማይችሉ ሊሰማቸው ይችላል።
2. **የሀብት ብክነት እና ብቃት አለመኖር፦** የማይገባቸውና ብቁ ያልሆኑ ግለሰቦች በነዚህ ስልጠናዎች ወይም ኮንፈረንስ ላይ ብሳተፉም ያገኙት እውቀት ወይም ክህሎት ተጠቃሚ ለመሆን የታሰበውን አደረጃጀት ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ላይተገበር ይችላል። ይህም የገንዘብና የድርጅት ሀብት እንዲባክን ያደርጋል።
3. **የሠራተኞች የሞራል ደረጃ መቀነስ፡-** ግዳዩ የሚገባቸው ግን የተዘለሉ ሰራተኞች ላይ የሞራል ደረጃ እንድቀንስ ያደርጋል። ሰዎች አድሎአዊነት ሲሰማቸው ጠንክረው የመሥራት ስሜታቸው ስለሚጎዳ የሥራ ተነሳሽነትን ሊያጡ ይችላሉ።
4. **የአደረጃጀት አቅም መዳከም፤** የድርጅቱ ወይም የማህበረሰቡ አጠቃላይ አቅም በአግባቡ ተከናውኖ ዓላማውን የማሳካት አቅም ይዳከማል። ምክንያቱም ሀብት ያለአግባብ ይባክናል። ግለሰቦች ውጤታማ በሆነ መንገድ የተማሩትን በሥራ ላይ ማዋል አይችሉም።

5. **የአንድን ተቋም መልካም ስም ይጎዳል**፡ - ይህ ድርጊት በውስጥም ሆነ በውጪ የተቋሙን ስም ያጎድፋል። የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በድርጅቱ ጽኑ አቋም ላይ ያላቸውን እምነት ያጣሉ። ይህም ወደፊት ተባብሮ መሥራትን ወይም የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት በምትችልበት አጋጣሚ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።
6. **የሙስና ባሕል እንዲስፋፋ ማድረግ**፡- እንዲህ ዓይነቶቹ ድርጊቶች ለሌሎች ምግባረ ብልሹ ድርጊቶች ምሳሌ ይሆናሉ። መሪዎች አድልዎ በሚፈጽሙበት ጊዜ ምግባረ ብልሹነት በቸልታ እንደሚታለፍ አልፎ ተርፎም እንደሚካስ ለሌሎች ያመለክታል፤ ይህም መርዛማ የሆነ ድርጅታዊ ባህል ይፈጥራል።

**ማስታወሻ**

ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች አንጻር ሲታይ እንደዚህ ዓይነት ድርጊት በመጀመሪያ ደረጃ የአንድን ሀገር አስተዳደርና ተጠያቅነትን ያዳክማል። ስልጠና ወይም ኮንፈረንስ ተሳትፎ ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች (ለምሳሌ፦ በሰላም ግንባታ ዙሪያ የባለሙያዎች የአቅም ግንባታን መሰረት ያደረገ) ክህሎቶችን ለማሻሻል ታስቦ ከሆነ የማይገባቸው ግለሰቦች እንዲሳተፉ መፍቀድ የመንግስት ወይም የግል አገልግሎቶችን አጠቃላይ ውጤታማነት ሊቀንስ ይችላል፣ በመጨረሻም የልማት እና የሰላም ግንባታ ጥረቶችን ያደናቅፋል። እንድሁም ፍትህን በማዛአባት እና ልዩነቶችን በመፍጠር የእኩልነት ንረት ይበልጥ እንዲጠናከር ምክንያት ይሆናል። ባጠቃላይ በአድልዎ፣ ወይም ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም ሀብትን በማባከን፣ ተቋማዊ አመኔታን በማዳከምና የድርጅቱን ገጽታ በማበላሸት ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል የሙስና ዓይነት ነው። ይህ ዓይነቱ ምግባረ ብልሹነት ፍትሃዊነትን ከማዳከም አልፎ የግለሰቦችንና የተቋማት የጸና አቋም እንድበላሽ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ሰፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ያስከትላል።

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ አስርጅ ናሙና ቀጥሎ ቀርቧል። አስረጅ ናሙናውን በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያዩበት።

## አስረጅ ናሙና 2

በ2016 ዓ.ም. የሰላም ሚኒስቴር የጸረ ሙስና ክፍል የመ/ቤቱን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተመለከተ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት በአንድ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቢቱ ወሳኝ ስራዎችን ለሚሰሩ ባለሙያዎች ወደ ውጭ ሀገር የጉዞ እድሎች ይፈጠርላቸዋል፡፡ የጉዞው ዋነኛ ዓላማ እነዚህ ባለሙያዎች ለሙያ እድገታቸውም ሆነ ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ አገልግሎት ዓላማ ስኬታማነት የሚጠቅሙ ልምዶችን እንድቀስሙ እና ዕውቀት እንዲያገኙ ታስቦ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ስልጣናቸውን ተገን በማድረግ ኃላፊው የጉዞ እድሉን ከማሳወቅ ይልቅ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች በመደበቅ ወይም በመከልከል እና ባለሙያዎቹ ከጉዞው ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ጉዞው የታሰበላቸውን ባለሙያዎች በማሳጣት ለራሱ ይወስዳል፡፡ በተጨማሪም ኃላፊው ጉዳዩ የማይመለከታትን የመስሪያቤቱን ፀሐፊ በጉዞው ላይ አብረዋቸው እንድጻተፍ በማድረግ ከፊተኛ የሆነ ገንዘብ ወይም ዶላር በማግኘትም ተጠቃሚ እንድትሆን አደረጉ፡፡

ከላይ የቀረበውን አስረጅ ናሙና መሰረት በማድረግ የሚክተሉ ጥያቄዎችን ተወያዩበት፡፡

1. በዚህ ጽሑፍ መሰረት የተፈጸሙ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ወንጀሎችን በመለየት እያንዳንዱን አብራሩ፡፡
2. ይህ ድርጊት ከስነ ምግባር ጉድለት፣ ከሕግ መተላለፍ፣ ከተአማንነት እና ከፋይናንስ አስተዳደር አንጻር የሚይስከትላቸው ተጽዕኖ በመወያየት አብራሩ፡፡
3. ይህ ድርጊት የመስሪያ ቤቱ አሰራር እና አጠቃላይ የገጺታ ግንባታን ልያበላሽ በሚችልበት ሁኔታ ላይ በመወያየት ግለጹት፡፡
4. ይህንን በተመለከተ በየደረጃው ለሚከሰቱ የሰራር ክፍተቶች እና የሙስና ወንጀሎች ልወሰዱ የሚገቡ የእርም እርምጃዎች መሆን አለባቸው ብላቹ ታስባላቹ? በመወያየት ግለጹ፡፡

ይህ ጉዳይ አድልዎ፣ የሃብት ብዝበዛና የመንግስትን ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ በሥነ ምግባር አስተዳደር እና በህዝብ አገልግሎት ውስጥ በመልካም መሰረት ላይ የተመሰረቱ እድሎችን ለማራመድ ተቋማዊ ተሀድሶዎች አስፈላጊ ስለመሆኑ አበረታች ውይይት ንዑስ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

## 2.10. በንብረት አስተዳደር ላይ የተስተዋለ ብልሹ አሰራርና ጉዳቶቹ

በዚህ ሁኔታ በህጋዊ መንገድ ለተሽከርካሪው ወሳኝ ተደርገው የሚቆጠሩ የተለያዩ የተሽከርካሪ ትርፍ ክፍሎች- ለምሳሌ የመኪና ጃክ (ክሪክ)፣ ባትሪ፣ መቀመጫ ሽፋን፣ ወለል ምንጣፍ፣ ሽፋኖች፣ ጎማዎች እና የመሳሰሉ ዕቃዎች- በህገ ወጥ መንገድ ተወስደዋል፡፡ እንደነዚህ ያሉትን ክፍሎች መጠቀም የንብረት አስተዳደር ሕጎችን የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የሕዝብ ሀብትን አላግባብ መጠቀም እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ እነዚህ ክፍሎች በሕጋዊ መንገድ ከተሽከርካሪው የማይለዩ በመሆናቸው፣ መወገዳቸው የንብረት አስተዳደር ፕሮቶኮሎችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጥስ ነው፡፡

# አስረጂ ናሙና 3

በሰላም ሚኒስቴር የጸረ ሙስና ክፈል በ2016 ዓ.ም. የሙስና ስጋት ተጋላጭነት አስመልክቶ ባካሄደው የዳሰሳ ጥናት መሰረት የመስክ ሥራ ላይ መሳተፍ የሌለባቸውን ሰዎች በመሳተፍ አበል እንድያገኙ ይደረጋል፡፡ ይህም በባለሙያ ፋንታ ለበዓል ስባል አመራር መስክ እንድሄድ እና ያልተገባውን ብር እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ አመራሩ ባለሙያዎችን በማሰማራት ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ሲገባው ባለሙያዎቹን በመከልከል በራሱ መስክ እንድሄዱ ተደርጓል፡፡ ይህ ማለት አመራሩ በአንድ ጊዜ እንደ ባለሙያም እንደ አመራርም ሆኖ እንደሰራ የዳሰሳ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ይህ በንዲህ እንዳለ ባንድም በሌላም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ክፍሎችም ይህንን እያወቁ አይቻልም ማለት ሲገባቸው መከልከልና መቃወም ሲገባቸው በዝምታ ተቀብለው ያስተናገዱ ሰራተኞችና ስራ ሃላፊዎችም እንደነበሩ ከተደረገው የዳሰሳ ጥናት ግኝት መረዳት ተችሏል፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች***

**ከላይ የቀረበውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ቀጦ የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡**

1. በዚህ ውስጥ በግልጽ የሚታዩ የሙስና ባሕርያት ወይም ዓይነቶችን ግለጹ፡፡
2. በዚህ ውስጥ የሚታዩ የስነምግባር እና ሕጋዊ ጥሰቶችን በመለየት አብራሩ፡፡
3. ይህ ድርጊት በመ/ቤቱ ሰራተኞች መልካም ግንኙነት እና አሰራር ላይ ልፈጥረው የሚችለውን ችግሮች በመለየት ግለጹ፡፡

## 2.11. ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ውስጥ በሰላም ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ ያሉ የተለያዩ የሥነምግባር ጥሰት እና የሙስና ወንጀሎች የተላያዩ አስረጅ ናሙናዎች በማካተት በጥልቀት ተዳሷል፡፡ የሙስና ወንጀል በአንድ ሀገር የኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራው፣ እና ፖለቲካዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ያሳድራል፡፡ እነዚህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚንጸባረቁ የተለያዩ የሙስና ወንጀሎች ሰፋ ባለ መልኩ ቀርቧል፡፡ ይህም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለበት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እና የሙስና ወንጀሎችን በተለያዩ ክፍሎች ለሰልጣኞች ለመወያየት ያመች ዘንድ ባስረጅ ናሙናዎች በማስደገፍ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## 2.12. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለቤቱ አቅርቡ፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ምን ዓይነት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ይንጸባረቃሉ?
- የሙስና ወንጀል በአንድ ሀገር አጠቃላይ እድገት ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖችን በመወያየት አብራሩ፡፡
- የሰላም ሚኒስቴር መ/ቤት ከተቋቋመለት ዓላማ አንጻር የተሰጠውን ሀገራዊ ኃላፍነቶችን በአግባቡ ይንዳይወጣው በይበልጥ እንቅፋት የሚሆኑበትን የውስጥ አሰራርና የውጭ ጫናዎችን በመለየት ከመፍትሄ ሃሳብ ጋር ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የዘርፎች የሙስና መከላከያ

### 3.1. መግቢያ

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.2. ዓላማ

**ሰልጣኞች የዚህን ክፍል ስልጠና ከወሰዱ በኋላ፤**

1. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
2. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
3. በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፣
4. የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
5. በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

### 3.3. ስልጠናው የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ፤

ስልጠናው 6፡00 ሰዓት ሊወስድ ይችላል፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
3. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

### 3.4. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

## 3.5. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

### 3.5.1. ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

### 3.5.2. ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራሁም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 3.5.3. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 3.5.4. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

### 3.5.5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### 3.5.6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሜይንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 3.5.7. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### 3.5.8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-

ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

### 3.5.9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

### 3.5.10. ማጠቃለያ

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን

በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄ**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
2. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

## 4. የግል መገምገሚያ ቼክ ሊስት

| 1. | የግል አቋም እና ስነ-ምግባር | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1.1. | የአገልግሎቱን የሥነምግባር ደንብና የሥነምግባር መመሪያዎችን ሁሌም እከተላለሁ:: | | |
| 1.2. | በባለስልጣንነት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የፍላጎት ግጭቶችን በሙሉ ይፋ አደረኩ:: | | |
| 1.3. | በውሳኔዎቼ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ስጦታዎችን፣ ሞገስን ወይም እንግዳ ተቀባይነትን ከመቀበል እቆጠባለሁ:: | | |
| 1.4. | በሁሉም የመገናኛ ዘዴዎቼና ሪፖርተሮቼ ላይ ግልፅና ሐቀኛ ነኝ:: | | |
| 1.5. | በየጊዜው ለግል ጥቅም ሳይሆን ለህዝብ የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን አደርጋለሁ:: | | |
| **2.** | **የፋይናንስ አስተዳደር** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 2.1. | የሚኒስቴሩን የገንዘብ ደንብና የግዥ ሂደት ጠንቅቄ አውቃለሁ:: | | |
| 2.2. | የምሳተፍባቸው የገንዘብ ልውውጦች በሙሉ የተመዘገቡ፣ግልፅና ኦዲት ያላቸው እንዲሆኑ አደርጋለሁ:: | | |
| 2.3. | የገንዘብ አያያዝን አላግባብ በመጠቀም፣ በመጠለፍ ወይም ገንዘብን አላግባብ በመጠቀም ረገድ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ከማድረግ እቆጠባለሁ:: | | |
| 2.4. | ማንኛውንም አለመጣጣም ወይም ልዩነት ለይቼ ለማወቅ አዘውትሬ የገንዘብ ነክ ጉዳዮችንና ሪፖርቶችን እመረምራለሁ:: | | |
| 2.5. | ማንኛውንም የጥርጣሬ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ወይም ስጋት ለተገቢው ባለስልጣናት ሪፖርት አድርጌያለሁ:: | | |
| **3.** | **ግዥና ውል** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 3.1. | ውል ስሰጥ ግልፅና ተወዳዳሪ የግብይት ሂደትን እከተላለሁ:: | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| 3.2. | ሁሉም ውሎች ያለአድልዎ ወይም ወገናዊነት በመልካምነት ላይ ተመስርተው እንዲፈጸሙ አድርጌያለሁ:: | | |
| 3.3. | በግዢ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት መጋጨት, ግብይት-rigging, ወይም kickbacks አስወግዳለሁ. | | |
| 3.4. | የኮንትራክተሮችን አፈጻጸም በመከታተል ከኮንትራት ውሎች ጋር ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ንቁ ነኝ:: | | |
| 3.5. | ማንኛውንም የግል ወይም የገንዘብ ግንኙነት ከጨረታ አጫራቾች ወይም ተቋራጮች ጋር ገልጫለሁ:: | | |
| **4.** | **የምልመላና የሰው ሀብት** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 4.1. | በመልካም እና ብቃት ላይ የተመሰረተ ፍትሃዊ እና ግልፅ የሆነ የምልመላ ሂደት ውስጥ እሳተፋለሁ:: | | |
| 4.2. | በቅጥር ወይም በማስተዋወቅ ውሳኔዎች ላይ ከማንኛውም ዓይነት የዘር ጥላቻ፣አድልዎ እርቃለሁ:: | | |
| 4.3. | ከሥራ አመልካቾች ወይም ከአሁኑ ሠራተኞች ጋር ማንኛውንም የግል ግንኙነት አስወግዳለሁ:: | | |
| 4.4. | ሁሉም የስራ እና የማስተዋወቂያ ሂደቶች በአግባቡ የተመዘገቡ እና ኦዲት ማድረግ የሚችሉ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ:: | | |
| 4.5. | ለሁሉም ሰራተኞች የስልጠናና የልማት እድል አበጅቻለሁ:: | | |
| **5.** | **ግራንት እና እርዳታ ስርጭት** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 5.1. | እርዳታን ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችንመሰረት በማድረግ እንዲከፋፈል አደርጋለሁ:: | | |
| 5.2. | ምንም ዓይነት ተፅዕኖ ወይም ግፊት በማስወገድ ገንዘብ ንዋያት ባልሆኑ ነገሮች ላይ ተመስርቶ እንዲከፋፈል አድርጌያለሁ:: | | |
| 5.3. | ስለእርዳታ እና የእርዳታ ስርጭት ሂደቶች ቋሚ ምርመራ እና ክለሳ እመራለሁ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5.4. | ገንዘቡ የታሰበውን ተጠቃሚ እየደረሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ትጉህ ነኝ | | |
| 5.5. | የስጦታ ገንዘብ አላግባብ ጥቅም ላይ የዋለ ወይም አላግባብ መከፋፈሉን ሪፖርት አድርጌያለሁ:: | | |
| **6.** | **የሰላም ድርድርና ሠፈር** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 6.1. | በሁሉም የሰላም ድርድርና ግጭቶችን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት የማያዳላና ፍትሃዊነትን ጠብቄያለሁ:: | | |
| 6.2. | የድርድሩን ውጤት ሊነካ የሚችል ማንኛውም ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖ ወይም ጉቦ አስቀርቻለሁ:: | | |
| 6.3. | ሁሉም የድርድር ሂደቶች ግልፅና ተያያዥ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን የሚያካትቱ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ:: | | |
| 6.4. | በድርድር ወቅት የደረሱ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን በሙሉ ለማስመዝገብ እጠነቀቃለሁ:: | | |
| 6.5. | በድርድር ወቅት ሊነሱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ለመፍታት ጥረት አድርጌያለሁ:: | | |
| **7.** | **መረጃ አስተዳደር** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 7.1. | ምሥጢራዊ እና ጥንቃቄ የተሞላበት መረጃን ያልተፈቀደ አግባብነት ወይም መገለጫ እጠብቃለሁ:: | | |
| 7.2. | ለግልም ሆነ ለውጪ ጥቅም ስል መብት ያገኘኋቸውን መረጃዎች ከመጠቀም እቆጠባለሁ:: | | |
| 7.3. | መረጃ ማጋራት ግልፅ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መሆኑን አረጋግጣለሁ:: | | |
| 7.4. | የኢንፎርሜሽን ጥሰትን ለመከላከል የኢንተርኔት ጥበቃ ተግባራትን በንቃት እጠቀማለሁ:: | | |
| 7.5. | መረጃን አላግባብ መጠቀም ወይም አላግባብ መጠቀም የሚጠረጠረውን ሪፖርት አድርጌያለሁ:: | | |
| **8.** | **ህጋዊ እና ስርዓት አፈፃፀም** | **አዎ** | **አይደለም** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8.1. | የሚኒስቴሩን አሠራር ስለሚቆጣጠር ህጋዊና አስተዳደራዊ ደንብ ዕውቀት አለኝ:: | | |
| 8.2. | ሁሉም ተግባራትና ውሳኔዎች ተግባራዊ የሆኑ ህጎች እና ደንቦች ጋር እንዲጣጣሙ አደርጋለሁ:: | | |
| 8.3. | ግልጽ ያልሆነ ወይም ውስብስብ የሆኑ የሕግ ጉዳዮች ሲያጋጥሙኝ የሕግ ምክር እጠይቃለሁ:: | | |
| 8.4. | ለግልም ሆነ ለተቋማዊ ጥቅም ሲባል ማንኛውንም የህግ ወንጀል ወይም መተላለፍ እርቃለሁ:: | | |
| 8.5. | ማንኛውንም ህጋዊ ወይም የህግ ጥሰት ለተገቢው ባለስልጣናት ሪፖርት አድርጌያለሁ:: | | |
| **9.** | **ተጠያቂነት እና ግልፅነት** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 9.1. | ስለእንቅስቃሴዎቼና ውሳኔዎቼ ለኃላፊዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዘወትር ሪፖርት አደርጋለሁ:: | | |
| 9.2. | ለምርመራና ለክለሳ መረጃዎችን እና መዝገቦችን ለማግኘት አስችያለሁ:: | | |
| 9.3. | በቡድኔና በአገልግሎት ውስጥ የግልጽነትና የግልጽነት ባህል እንዲኖር አበረታታለሁ:: | | |
| 9.4. | በህዝብ ወይም በበላይተመልካች አካላት ለተነሱ ጥያቄዎችና ስጋቶች ምላሽ እሰጣለሁ:: | | |
| 9.5. | የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን አፈጻጸም ለመከታተልና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ አሠራሮችን አቋቁሚያለሁ:: | | |
| **10.** | **ሪፖርት ማድረግ እና ማፏጨት** | **አዎ** | **አይደለም** |
| 10.1. | በአገልግሎት ውስጥ ሙስናን ወይም ሥነምግባር የጎደለው ድርጊትን ሪፖርት ለማድረግ ተገቢ የሆኑ ቻናሎችን አውቃለሁ:: | | |
| 10.2. | የበቀል እርምጃ መውሰድ ሳይፈራ ማንኛውም የታዘበ ወይም የተጠረጠረ ሙስናሪፖርት አድርጌያለሁ:: | | |
| 10.3. | ሙስናን ወይም ጥፋትን ሪፖርት የሚያደርጉ ሰዎችን እደግፋለሁ እና እጠብቃለሁ:: | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10.4. | በጥበቃ ላይ ሚኒስቴሩ የሚኖራቸዉን ፖሊሲዎች አውቃለሁ፡፡ | | |
| 10.5. | ሥነምግባር የጎደለው ድርጊትን ሪፖርት ለማድረግ አስተማማኝና ድጋፍ ሰጪ ሁኔታ እንዲኖር አስተዋጽኦ አድርጌያለሁ፡፡ | | |

# ማጣቀሻ

Aidt, T. S. (2003). Economic analysis of corruption: A survey. The Economic Journal, 113, 632-652. http://dx.doi.org/10.1046/j.0013-0133.2003.00171.x.

Andrew, H. Y. (2003). Anti-Corruption Strategy of the Hong Kong Special Administrative Region of the People‟s Republic of China. Presentation held at the 4th Regional Anti-Corruption Conference in Kuala Lumpur, Malaysia on 3-5 December 2003.

Belloni, R., & Strazzari, F. (2014). Corruption in post-conflict Bosnia-Herzegovina and Kosovo: A deal among friends. Third World Quarterly, 35, 855-871. http://dx.doi.org/10.1080/ 01436597.2014.921434.

BMZ et al. 2019. Outcome document on results of the 'Anti-Corruption in Fragile States' conference. International Conference on Anti-corruption in Fragile States. Berlin, 5 November.

Cheng, C. S & Zaum, D. (2013) (eds). Corruption and Post-Conflict Peacebuilding. Routledge.

Chibwana C. (2008). Leadership enhancement in agriculture. USA. University of California.

Degye, G., Arega, Sh., & Demirew, G. (2024). Who is Corrupt in Ethiopia: Policy Working Paper 24/2024.

Findlay, M. and Stewart, M. (1991). Implementing Corruption Prevention Strategies through Codes of Conduct. Current Issues in Criminal Justice, 3, (2), 250-264.

GIZ. 2020. Anti-corruption in fragile settings: A review of the evidence.

Global Peace Index (2015). Peace and corruption. New York: Institute for Economics and Peace.

Heilbrunn, J. (2004). Anti-corruption commissions: Panacea or real medicine to fight corruption World Bank, Washington DC USA.

Hopp-Nishanka, U. 2021b. Corruption and conflict. Breaking the vicious circle from a peacebuilding perspective. FriEnt Working Group on Peace and Development.

ICAC (2009). Independent Commission against Corruption. Report on Corruption in the provision and Certification of Security Industry Training.

Kebede, G. 2013. Political Corruption: Political and Economic State Capture in Ethiopia. European Scientific Journal Vol.9, No.35 ISSN: 1857-7881. 23 October 2018.

Klitgaard, R. (1988) Controlling Corruption. University of California Press, Berkeley.

Lindberg, J., & Orjuela, C. (2014). Corruption in the aftermath of war: An introduction. Third World Quarterly, 35, 723-736. http://dx.doi.org/10.1080/01436597.2014.921421.

Mail and guardian Extent of publication Vol. 11, no. 21 (May 19 to 25, 1995)- Subjects Johannesburg (South Africa) — Newspapers.

Mauro, Paolo (1995). Corruption and Growth Quarterly journal of economics, 110.3.

Neudorfer, N. S., & Theuerkauf, U. G. (2014). Buying war, not peace: The influence of corruption on the risk of ethnic war. Comparative Political Studies, 47, 1856-1886. http://dx.doi.org/10.1177/0010414013516919.

Quah, Jon S.T. 2001. Curbing Corruption in Asia: A Comparative Study of Six Countries. Singapore: Eastern Universities Press.

Sáez-Martí, **María** (**2002**). On the cultural transmission of **corruption**. Journal of Economic Theory, 107(2):311-335.

Shimelis, A. (2005). Corruption and Anti-Corruption in Ethiopia: A case study of the Ethiopian customs authority MA Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.

Svensson, J. (2005). Eight questions about corruption. The Journal of Economic Perspectives, 19, 19-42.

The United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC); in the United Nations

Office at Vienna, 2004.

TRANSPARENCY INTERNATIONAL SECRETARIAT IMPLEMENTATION REPORT. Alt-Moabit 96 10559 Berlin Germany, 2013.

United Nations Convention Against Corruption (UNCAC), UNITED NATIONS New York, 2003.

Wing-chi, H. (2004). Combating Corruption: The Hong Kong Experience. Tsinghua china Law Review, 6(239), 239-256.

Zemelak Ayitenew Ayele, Corruption in Ethiopia: A Merely Technical Problem or a Major Constitutional Crisis? Conference Paper, September 2017 accessed on 02 October 2019.

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et